የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ኤምባሲ
ኦታዋ
EMBASSY OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
OTTAWA

ቀን 08/1/2018
ቁጥር ETEO-02/02/006/11

**ለሁሉም በካናዳ ለሚገኙ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ማህበራት አመራሮችና አባላት**

**<u>ባሉበት</u>**

**ጉዳዩ፡-** <u>የኢትዮጵያ የዳያስፖራ ትረስት ፈንድን ይመለከታል</u>

ክቡር ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አህመድ በቀን 1 ዶላር ለተለያዩ የልማት ሥራዎች በተለይም ለንጹህ የመጠጥ ውሃ ግንባታ፣ ለትምህርትና ለጤና ድጋፍ እንዲያደርጉ በዓለም ላሉ ዳያስፖራ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ጥሪ ማቅረባቸዉ ይታወቃል። ይህንን ጥሪ ተግባራዊ ለማድረግ ከዳያስፖራው የተወጣጡ ምክር ሰጪ ካውንስል ምክር ቤት በማቋቋም የዳያስፖራ ትረስት ፈንዱን እንዲመሩ የተደረገ ሲሆን ካውንስሉ ለሕዝብ መዋጮ መሰብሰቢያ ያዘጋጀውን ዝግጅት ለሕዝብ ይፋ አድርጎ ሥራውን በኦፊሴላዊ ድረ-ገፅ https://www.ethiopiatrustfund.org መጀመሩ ይታወቃል፡፡ በዚሁ መሠረት የትረስት ፈንድ ሥራ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ተሳትፎ እያደረጉ ቢሆንም በርካታ ኢትዮጵያዊያን ለትረስት ፈንዱ መዋጮ አከፋፈል ረገድ የመረጃ እጥረት እንዳለባቸው በስልክና በአካል ለኤምባሲያችን ገልፀዋል፡፡

ስለሆነም በካናዳ ሀገር ለምትገኙ ሁሉም ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን የዲያስፖራ አባላት ለፈንዱ ድጋፍ መስጠት የምትፈልጉ ከላይ በተጠቀሰው ድረ-ገፅ በመግባት **"Donate Now"** የሚለውን በመጫን በCredit card/ Apple pay/ Google Pay/ PayPal/ በመጠቀም በ"online" በቀጥታ ማስተላለፍ ትችላላችሁ። በሌላ አማራጭ ደግሞ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ Ethiopian Diaspora Trust Fund ስም በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000255726725 የባንክ የስዊፍት ኮድ አድራሻ CBETETAA ከኢትጵያ ንግድ ባንክ ጋር ስምምነት ባላቸው ባንኮች ወይም ዝርዝራቸዉ ከታች በቀረቡት ፈጣን የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶችን በመጠቀም ከላይ በተጠቀሰው የባንክ ሂሳብ ቁጥር የድጋፍ ገንዘቡን መላክ የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡ በትረስት ፈንዱና በሌሎች የዳያስፖራ ጉዳዮች ላይ ተጨማሪ መረጃና ማብራሪያ የምትፈልጉ በኦታዋ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ኤምባሲ አቶ መርጋ ፈይሳን በስልክ ቁጥር (613) 565 6637 ext **213** በኢሜል Merga.Tufa@ethioembassycanada.org፣ አቶ ፈለቀ መኮንን በስልክ ቁጥር (613) 565 6637 ext **207** እንዲሁም አቶ ፍስሀ ዘሪሁን በስልክ ቁጥር (613) 565 6637 ext **204** በመደወል መጠየቅ የምትችሉ መሆኑን ለመግለፅ እንወዳለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

**መርጋ ፈይሣ ቱፋ**
**ሚኒስትር**
**ዲያስፖራ ጉዳዮች ዘርፍ ሃላፊ**

አባሪ፡-

- ከኢትጵያ ንግድ ባንክ ጋር ስምምነት ያላቸው ፈጣን የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች ዝርዝር
- ትረስት ፈንዱን የተመለከተ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መግለጫ፣

#1501- 275 Slater St., Ottawa, Ontario, Canada K1P 5H9
Tel: (613) 565-6637 Fax: (613) 565-9175
Web site: www.ethioembassycanada.org
Email: info@ethioembassycanada.org

## ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር ስምምነት ባላቸው ፈጣን የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች

| | |
|---|---|
| 1. Western Union | 11. Lari Exchange |
| 2. X-Press Money Service | 12. Tewkel Money |
| 3. Bole Atlantic International | 13. Zenji Exchange Company |
| 4. Money Gram | 14. Paco Money |
| 5. Dahabshiil Money Transfer | 15. Irmaan Express |
| 6. Al Ansari (Cash Express) | 16. Bakkal Money Transfer |
| 7. World Remit Ltd | 17. Devine (Blue Nile) |
| 8. Trans Fast Money | 18. Dawit Money Transfer |
| 9. Kaah Express Money Transfer | 19. T and Y Remit |
| 10. Golden Money Transfer | 20. Asgori Money Express |
| | 21. World Remit Money Transfer |

# የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ትረስት ፈንድ

በሁለንተናዊ የሀገራችን ልማት ውስጥ የዳያስፖራው ማኅበረሰብ የሚያበረክተውን ወሳኝ አስተዋጽኦ ለማጠናከር የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግስት ለኢትዮጵያ ዳያስፖራ ማኅበረሰብ የድጋፍ ጥሪ ማድረጉ ይታወቃል። ጥሪውን ተከትሎ በርካታ የዳያስፖራው ማኅበረሰብ አባላት አስደሳች ምላሽ በመስጠት ላይ ናቸው።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በበኩሉ የገንዘብ ድጋፍ ሂደቱን ለማቀላጠፍ Ethiopian Diaspora Trust Fund በሚል ስም በባንኩ ዓለም አቀፍ አገልግሎት ልዩ ቅርንጫፍ የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ቁጥር 1000255726725 በመክፈት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

በመሆኑም ለዚህ አገራዊ በጐ አድራጐት ድጋፍዎን ለማድረግ የሚከተሉትን አማራጮች መጠቀም ይችላሉ።

- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሆነው የስዊፍት አድራሻ CBETETAA፤
- ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር በሚሠሩ ዓለም አቀፍ የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች አማካይነት።

መንግስት በገባው ቃል መሠረት በየቀኑ የምትለግሱት ገንዘብ ተጠራቅሞ ለሆስፒታልና ለትምህርት ቤት ግንባታ እንዲሁም ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት የሚውል በመሆኑ የወገኖቻችንን መሠረታዊ ችግሮች በመቅረፍ ረገድ ትልቅ ትርጉም አለው።

የሚሰበሰበው ገንዘብ ራሱን በቻለ ቦርድ የሚተዳደር በመሆኑም ለታሰበለት ዓላማ ለመዋሉ ጥብቅ ክትትል ይደረግበታል።

አድራሻ: ጋምቢያ ጎዳና
ስልክ: +251-11-551-95-06 +251-11-551-50-04